# መጽሐፍ ቅዱስ ለህፃናት
## አቅራቢዎች



# የእግዚአብሔር መልዕክተኛ

ጸሐፊው: Edward Hughes
የተተረጎመው: Abel Eshetu
ምሣሌ አቅራቢው: Byron Unger; Lazarus
ያሻሸለው (አሻሸሎ የጻፈው): E. Frischbutter; Sarah S.

ታሪክ 37 ከ 60 ዎቹ መሃከል

www.M1914.org

***Bible for Children,*** *PO Box 3, Winnipeg, MB R3C 2G1 Canada*

ፈቃድ፥- ይህንን የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪክ ማባዛት ወይም ማተም ይቻላል
ነገር ግን ይህ መሆን የሚችለው ለሽያጭ ካላቀረባችሁ ብቻ ነው።

አማርኛ

Amharic

ሽማግሌው ካህን ዘካሪያስ በቤተመቅደስ ውስጥ ዕጣን ያጥን ነበር።ሕዝቡ ሁሉ በውጭ ቆመው ይጸልዩ ነበር።የጌታም መልአክ በዕጣኑ መሠዊያ ቀኝ ቆሞ ታየው።ዘካርያስም በድንገት ደነገጠ፥ ፍርሃትም ወደቀበት።



1

መልአኩም እንዲህ አለው፦ ዘካርያስ ሆይ፥ ጸሎትህ ተሰምቶልሃልና አትፍራ።ሚስትህ ኤልሳቤጥም ወንድ ልጅ ትወልድልሃለች፥ ስሙንም ዮሐንስ ትለዋለህ።



2


ገናም በእናቱ ማኅፀን ሳለ መንፈስ ቅዱስ ይሞላበታል።
3


በውጭ ያሉት ሰዎች ዘካሪያስ ዲዳ በመሆኑ ተገርመዋል። መልዓኩ ገብርኤል በጊዜው የሚፈጸመውን ቃሌን ስላላመንህ፥ ይህ ነገር እስከሚሆን ቀን ድረስ ዲዳ ትሆናለህ መናገርም አትችልም ያለውን አላወቁም ነበርና።ሚስቴ ስላረጀች ልጅ መውለድ አንችልም ብሎ ነበር።
4


ዘካሪያስ እግዚአበሔር የተናገረውን ሁሉ ማስታወሻ ይጽፍ ነበር።ሚስቱ ኤልሳቤጥ ሁልጊዜ ይገርማት ነበር። ስለ ልጅ ሁል ጊዜ ይጸልዩ ነበር።
5


ኤልሳቤጥም እንደፀነሰች አወቀች። እግዚአብሔርን አመሰገነች። ዘመድዋ ማርያምም አንድ ቀን ልትጠይቃት ወደ ቤቷ መጣች። ማርያምም ፀንሳ ነበር።
6


ኤልሳቤጥም የማርያምን ሰላምታ በሰማች ጊዜ ፅንሱ በማኅፀንዋ ውስጥ ዘለለ፤ በኤልሳቤጥም መንፈስ ቅዱስ ሞላባት፥ የማርያም ልጅ ጌታ ክርስቶስም እንደሚሆን ታውቅ ነበር።ሁለቱ ሴቶች በአንድነት እግዚአብሔርን አመሰገኑ።
7


ኤልሳቤጥም ልጇን ወለደች። ካህናቱ በአባቱ ስም ዘካርያስ ሊሉት ወደዱ።እናቱ ግን መልሳ። አይሆንም፥ ዮሐንስ ይባል እንጂ አለች። አባቱም ስሙ ዮሐንስ ነው ብሎ ጻፈ።ያንጊዜም አፉ ተከፈተ መላሱም ተፈታ እግዚአብሐርንም እየባረከ ተናገረ።
8


ዮሐንስ ሲያድግ ልክ እንደ
እግዚአብሔር ሰው ኤልያስ
ነበር።የእግዚአብሔር ልጅ
ኢየሱስ ሊባርካቸው
እንደሚመጣ ለሕዝቡ
ይናገር ነበር።ንስሐ ግቡ!
9


ከኃጢአታችሁ
ተመለሱ! ይላቸው
ስለነበር የአይሁድ
መሪዎች ዮሐንስን
ይጠሉት ነበር።
10


የንስሐ ጥምቀት ያጠምቃቸው ስለነበር
አንዳንዶች መጥምቁ ዮሐንስ ብለው
ይጠሩት ነበር። አንድ ቀን ኢየሱስ
በዮሐንስ ሊጠመቅ መጣ።ዮሐንስ
ግን በእኔ አትጠመቅም
አለው። ኢየሱስ ግን
ግድ አለው።
ዮሐንስም
እሺ አለና
አጠመቀው።
11


ኢየሱስ ወዲያው ከውኃው
በወጣ ጊዜ ሰማያት
ሲቀደዱ መንፈስም እንደ
ርግብ ሲወርድበት አየ።
የምወድህ ልጄ አንተ
ነህ፥በአንተ ደስ ይለኛል
የሚል ድምፅ ከሰማያት
መጣ። ዮሐንስ ኢየሱስ
የዓለምን ኃጢአት
የሚያስወግድ
የእግዚአብሔር በግ
እንደሆነ ያውቃል።
12


ዮሐንስ ብዙዎችን ወደ እግዚአብሔር መልሶ ነበር።ሄሮድስ
የወንድሙን ሚስት ሄሮድያዳን ስላገባት ዮሐንስ ገሰጾት ነበር።
ዮሐንስ ጻድቅና ቅዱስ ሰው
እንደሆነ ሄሮድስ ቢያውቅም
ኃጢአቱን መተው ግን
አልፈለገም።ዮሐንስም
ስለ ጽድቅ መስበኩን
አልተወም። በዚህም
ምክንያት ይህ አመጸኛ
ገዥ ዮሐንስን እስር
ቤት ከተተው።
13


ሄሮድስም በተወለደበት ቀን የሄሮድያዳ ልጅ
ገብታ ስትዘፍን ሄሮድስንና ከእርሱ ጋር
የተቀመጡትን ደስ አሰኘቻቸው።የመንግሥቴ
እኩሌታ ስንኳ ቢሆን የምትለምኚውን ሁሉ
እሰጥሻለሁ ብሎ ማለላት።
14



ወጥታም ለእናትዋ። ምን ልለምነው? አለች። እርስዋም፦ የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ አለች። ሄሮድያዳ ዮሐንስን ትጠላው ነበር።

15

ወዲያውም ፈጥና ወደ ንጉሡ ገብታ። የመጥምቁን የዮሐንስን ራስ በወጭት አሁን ልትሰጠኝ እወዳለሁ ብላ ለመነችው።



16

ንጉሡም እጅግ አዝኖ ስለ መሐላው ስለ ክብሩ ሲል ሊከለክላት አልወደደም። ወዲያውም ንጉሡ ወታደሩን ልኮ ራሱን እንዲያመጣ አዘዘው። ሄዶም በወኅኒ ራሱን ቈረጠ።



17

ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው መጡ የጻድቁንና የታማኙን አገልጋይ በድን ወስደው ቀበሩት። ዮሐንስ ተልዕኮውን ፈጽሞ ሄዷል። ኢየሱስም ከሀዘናቸው እንደሚያጽናናቸው ደቀመዛሙርቱ ሳያስቡ አልቀረም።



18

የእግዚአብሔር መልዕክተኛ

ይህ ታሪክ የሚገኘው የእግዚአብሔር ቃል በሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ

የማርቆስ ወንጌል 6
እና የሉቃስ ወንጌል 1 እና 3

“የቃልህ ፍቺ ያበራል.”
መዝሙረ ዳዊት 119:130

ክፉ ነገሮችን እንዳደረግን እግዚአብሔር ያውቃል፣ ኃጢአት ብሎም ይጠራዋል።

እግዚአብሔር እጅግ በጣም ስለወደደን አንድያ ልጁን ለመስቀል ሞት አሣልፎ በመስጠት የኃጢአትን ዋጋ በሞቱ ከፍሎልናል። ኢየሱስ ህያው ሆኖ ከሞት መነሣት ወደ ሠማይ አርጓል። አሁን እግዚአብሔር ኃጢአታችንን ይቅር ይለዋል።

ከኃጢአታችሁ ለመመለስ ከወሰናችሁ ለእግዚአብሔር እንዲህ በሉት። እግዚአብሔር አምላክ ሆይ ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኔ ኃጢአት ሲል እንደሞተና አሁን ህያው ሆኖ እንዳለ አምናለሁ። እባክህ ወደ ህይወቴ ግባና ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል ስለዚህ አዲስ ህይወት ይኖረኛል ደግሞ ከአንተ ጋር ለዘላለም እኖራለሁ። ጌታ ሆይ እንደ ልጅ ለአንተ እንድኖርልህ እርዳኝ አሜን። ዮሐ. 3.16